# “በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም”

**ያዕቆብ በኃይሉ**

**(ክፍል አንድ)**

### ❖ አቆጣጠሮቹ በሙሉ እ.ኤ.አ ናቸው

*ይህ እማኝነት የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ አይደለም–በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የኤርትራንና የሶማሊያን ጉዳይ እንዲያጠና የተሰየመው ገለልተኛ አጣሪ ቡድን ያቀረበው ዘገባ እንጂ። ቡድኑ በቅርቡም የአስመራው መንግስት ከሶማሊያው የሽብር ቡድን ጋር ያለውን ቁርኝት አለማቆሙን በድጋሚ ለፀጥታው ምክር ቤት አቅርቧል። ምክር ቤቱም የአጣሪ ቡድኑ የስራ ዘመን እንዲራዘም አድርጓል። እርግጥም አጣሪ ቡድኑ ነገ ስለ አቶ ኢሳያስ አስተዳደር የአሸባሪዎች አጋፋሪነትና አጋዥነት ምን እንደሚለን የሚወስነው ጊዜ ቢሆንም፤ እኔ “በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም” የሚል ርዕስ የሰጠሁትን የትናንት ማንነቱን ግን እንዲህ ዘክዝኮ አቅርቦታል።...*

*...ኤርትራ በይፋ ከኢትዮጵያ ተነጥላ ነጻነቷን ያወጀችው የወታደራዊው መንግሥቱ ኃይለማርያም አገዛዝ (ደርግ) በ1991 ያስወገደውን የ30 ዓመታት የነጻነት ትግል ተከትሎ በ1993 በተደረገው ህዝበ ውሳኔ ነው፡፡ በዓለም ባንክ ግምት 5 ነጥብ 1 ሚሊዮን ህዝብ እንዳላት የሚነገርላት ኤርትራ፤ ከዓለማች በኋላ ቀር ሀገሮች ተርታ ትፈረጃለች፡፡ ኤርትራ ከነጻነት ማግስት ጀምሮ ከጎረቤቶቿ ጋር ያላት ግንኙነት በፀብ አጫሪነት የተሞላ ነው፡፡*

*ድንበሯን በማካለሉ ሂደት ከኢትዮጵያ፣ ከየመንና ከጅቡቲ ጋር ጦርነት ከፍታለች፡፡ ከሱዳን ጋር ያላት ግንኙነትም ቢሆን ውስብስብና ሚናውን ያልለየ ነው፡፡ በጥር 2009 የሶማሊያ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎችን በመርዳትና ከጅቡቲ ጋር በፈጠረችው የድንበር ግጭት በቀረበባት ክስ ምክንያት የፀጥታው ምክር ቤት ኤርትራን አስመልክቶ በቁጥር 1907 (2009) የማዕቀብ ውሳኔ አስተላልፋል። ሁለተኛውንም ማዕቀብ ከአራት ዓመታት በፊት ጥሎባታል።*

እነዚህ ማዕቀቦች በኤርትራ ላይ አጠቃላይ የጦር መሣሪያ እገዳን (መሸጥ፣ መለወጥ፣ መጠቀም) አለመቻልን ያወጀ ሲሆን፤ በቀጣናው ያሉ ታጣቂ ኃይሎችን እንዳትረዳም የሚከለክል ነው፡፡ ህጉን የሚጥሱ አካላት የጉዞና በባንክ ያለ ገንዘባቸውን ያለማንቀሳቀስ እገዳ ይጥልባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛው ማዕቀብ የፀጥታው ምክር ቤት የአስመራው አስተዳደር ውጪ ከሚገኙ ዜጎቹ የሚሰበስበውን የሁለት ከመቶ የቀረጥ ታክስ እንዳይወስድ የሚያግድ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

ኤርትራ በቀጣናው ከሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ጋር ያላትን ንክኪ ጨምሮ የውጭና የደህንነት ፖሊሲዋ ከ1998 እስከ 2000 ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር ካደረገችው ጦርነት አንጻር ብቻ ሊጤን የሚገባው ይመስላል፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር አካላይ ኮሚሽን ውሳኔን ኢትዮጵያ አለማክበሯ፣ የሲቪልና ወታደራዊ ሃይሎች ዛሬም ድረስ በአካባቢው እንደሰፈሩ መቅረታቸው፣ ኤርትራ ኦብነግንና ኦነግን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ታጣቂ ሃይሎችን ለመርዳቷ ምክንያት አድርጋ ታቀርባለች፡፡

ኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ማድረጋቸው የኤርትራን ፖለቲካዊና የልማት መዘውር አቅጣጫውን እንዲቀይር አስገድዶታል፡፡ ኤርትራ በ1997 ያረቀቀችው ህገ - መንግስት እንዲቆም አድርጎታል፡፡ ምርጫ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዝሟል፡፡ የኤርትራ ገዥው ፓርቲ ህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ለፍትህ (ህግደፍ) ራሱን ወደ ወታደራዊ ግንባር ቀይሮ፤ የመንግስት አስተዳደርንና ተግባራቱን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል፡፡ እናም የመንግስትና የፓርቲ ተቋማት ተደበላልቀዋል፡፡ ስልጣንና ሀብት በጥቂቶች እጅ ወድቋል። የመንግስት ተቋማት የሚመሩት በዘፈቀደ ነው፡፡

በዚህ ዘገባ የተገለጹትን የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1844 (2008) እና 1907 (2009) ጥሰት ተጠያቂዎችና ግለሰቦች ለማጣራት፤ አጣሪ ቡድኑ ከሀገሪቱ አስተዳዳሪዎች፣ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች የደህንነትና የፓርቲ ባለስልጣናት ጋር ለመገናኘት ችሏል፡፡ ፍጹም ግለሰባዊነት የሰፈነበት የውሳኔ አሰጣጥ፣ ዘፈቀዳዊ የሆነ የሀብት አጠቃቀምና ብክነት እንዲሁም ልማዳዊ አሰራሮችና ማን አለብኝነት መንሰራፋታቸውን አጣሪ ቡድኑ ተገንዝቧል፡፡ አጣሪ ቡድኑ በዚህኛው የሥራ ዘመኑ በጅቡቲ፣ በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በሱዳን የሚንቀሳቀሱትን ጨምሮ በቀጣናው ያሉ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎችን ኤርትራ እንደምትደግፍ አሳማኝ መረጃ አሰባስቧል፡፡

በኬንያ፣ በኡጋንዳ፣ በዩናይትድ አረብ ኢሚሬትስና በሌሎችም አካባቢዎች የሚኖሩ የኤርትራ የዲፕሎማሲ ፣ የደህንነትና የህግደፍ ደጋፊዎች ለተጠቀሱት ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ አል-ሸባብን ጨምሮ ከሌሎች ታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር ግንኙነት መመስረቱን የኤርትራ መንግስት አልካደም፡፡ ይሁንና ግንኙነት ፖለቲካዊ እንጂ ወታደራዊ የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍን እንደማያካትት አስተባብሏል፡፡

አጣሪ ቡድኑ ያሰባሰባቸው የገንዘብ ክፍያ ደረሰኞች እንዲሁም ከአብዬሽንና ከባህር ላይ ጉዞ ቀጥተኛ ትስስር ካላቸው የዓይን እማኞች ጋር የተደረጉ ቃለ መጠይቆች ሁሉ እንደሚያመላክቱት፤ ኤርትራ ከሶማሊያ ታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር የነበራት ግንኙነት ከሰብዓዊና ፖለቲካዊ ሃይሎች ጋርም ይሁን ከአል-ሸባብ ጋር በእርቀ ሠላምና በድርድር ጉዳዮች ዙሪያ በተናጠልም ሆነ በቡድን የተሳተፈችባቸው የፖለቲካ መድረኮች ስለመኖራቸው ማረጋገጫ አልተገኘም፡፡

ኤርትራ የኢትዮጵንና የጅቡቲን ታጣቂ ቡድኖች ስለመርዳቷ ለቀረበላት ጥያቄ የሁለት ሀገሮች ውዝግብ ከድንበር ጋር የተገናኘ መሆኑን ካስታወሰች በኋላ ከጅቡቲ ጋር የተፈጠረውን የድንበር ውዝግብ ለመፍታት ግን በኳታር አደራዳሪነት ጉዳዩ ለእርቅ መቅረቡን በመጥቀስ ለአጣሪ ቡድኑ መረጃ ለመስጠት አልፈቀደችም፡፡

የአስመራው መንግስት ለታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎች የምታደርገው ድጋፍ የሚመራው ከብሔራዊ የደህንነት ጽሕፈት ቤት፣ ከኤርትራ ወታደራዊና ከህግደፍ (ህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ለፍትህ) አመራሮች በተውጣጡ አነስተኛ መኮንኖች በተመሰረተ ቡድንና በቀጥታ በፕሬዚዳንቱ ጽሕፈት ቤት አዛዥነት ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት በባህሪያቸው ምስጢራዊነት አልፎ አልፎ ደግሞ የኃላፊነት መደራረብ ይስተዋልባቸዋል፡፡የሥልጣን መባለግና ግለ-ታማኝነትም ሌላኛው መገለጫቸው ነው፡፡ ይህም የዕዝ ሰንሰለቱን ለማወሳሰብ ሆነ ተብሎ የሚሸረብ ሴራ ነው፡፡ መኮንኖቹ በርካታ ተግባራትን እንዲከውኑ ይጠበቃል፡፡ ከአንድ በላይ ለሆኑ የዕዝ ሰንሰለቶችም ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

የኤርትራ ደህንነት አገልግሎት መዋቅሩን ይበልጥ ለማወሳሰብ ደግሞ የማደራጀት ሥራ በመስራት ላይ መሆኑን በቅርቡ ለአጣሪ ቡድኑ የደረሱ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የሆነ ሆኖ ግን፤ ኤርትራ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የመታካሄደውን የውጭ ዘመቻዎችን የሚመሩና

አቅጣጫ በመስጠት ተግባር የተሰማሩ ዋና ዋና መኮንኖችን ቁልፍ ተልዕኮቻቸውን አጣሪ ቡድኑ ለማወቅ ችሏል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ብርጋድየር ጄኔራል ጠዓመ ጎይቶኦም ክንፉ (ወዲ መቀሌ) ነው። በአብዛኛው "ጠዓመ" ወይም "ወዲ መቀሌ" እየተባለ የሚጠራው ይህ ግለሰብ፤ ለሶማሊያ ታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎች ድጋፍ እንደሚያደርግ ቀደም ባሉት የአጣሪ ቡድኑ ዘገባዎች ተጠቁሟል፡፡ ወዲ መቀሌ ኤርትራ በአፍሪካ ቀንድ ለምታደርገው የውጭ ደህንነት ዘመቻ ዋና አዛዥ ነው፡፡ አጣሪ ቡድኑ የግለሰቡን ፎቶ ግራፍ ያገኘ ሲሆን፤ እሱነቱን ትክክል መሆኑንም አረጋግጧል፡፡

ሌላኛው ደግሞ ኮሎኔል ፍጹም ይሰኛል። ይህ ግለሰብ የጣዕመ ምክትል በመሆን የውጭ ዘመቻዎችን ይመራል፡፡ በቀጣናው የሚደረጉ የታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎች ስልጠናንም ይከታተላል፡፡ በኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች ታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎች ስልጠናም በቀጥታ ይሳተፋል፡፡ ኮሎኔል ፍጹም ከዚህ በተጨማሪም የምዕራባዊ ቀጣና እና ድንበር አዋሳኝ አዛዥ ለሆነው ጄኔራል ተክላይ ክፍሌ (ማንጁስ) ሪፖርት ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ከዚሁ ጄኔራል ጋር በድንበር አቋራጭ ህገ- ወጥ የንግድ ዝውውር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡

ሌላኛው ኮሎኔል ተወልደ ሃብቴ ነጋሽ ይባላል። ይህ ሰው "ሙሣ"፣ "አማኑኤል ኪዳኔ" እና "ወዲ ኪዳነ" በመሳሰሉት የሃሰት ስሞች ይታወቃል፡፡ ኮሎኔል ነጋሽ ከጠዓመ ጋር በቅርበት የሚሰራ ሲሆን፤ የሶማሊያ ታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖችን ለማሰልጠን የተመደበ ነው፡፡ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ታጣቂ ተቃዋሚ ሃይሎችንም በማሰልጠን ተሳትፎ አድርጓል። የፈንጅ ዕውቀት እንዳለውም ይነገርለታል፡፡ ከኬንያ ከአንድ ጊዜ በላይ የተባረረ ሰው ነው። ኮሎኔል ገመቹ አያናም እዚህ ላይ ይጠቀሳል። ኮሎኔል ገመቹ ኦነግን ለማሰልጠንና ድጋፍ ለመስጠት የተመደበ ነው።

ኮሎኔል ሃፃይነትም ማዕከሉን በምስራቅ ኤርትራ (ኪሎማ አካባቢ) ያደረገው የቀጣናው ወታደራዊ ደህንነት አዛዥ መኮንን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአፋርና ሶማሊያ ተቃዋሚ ቡድኖችን በማሰልጠንና በመርዳት ስራ ላይ ተሰማርቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በስለላ ስራ የተሰማሩ ባለስልጣናት አሉ። አንዱ ተስፋልደት ተክላይ ስላሴ ይባላል። ይህ ግለሰብ በፕሬዚዳንቱ ጽህፈት ቤት ዋና ሃላፊ ነው፡፡ ከፕሬዚዳንቱ ጋር የሚደረጉ

ግንኙነቶችን ይቆጣጠራል፡፡ የፕሬዚዳንቱን መመሪያዎችና ትዕዛዞች ለመንግስት የፓርቲ ባለሥልጣናትና የደህንነት ተቋማት ያስተላልፋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ወክሎ የውጭ ተልዕኮዎችንም ይከውናል፡፡ ጄኔራል ተክላይ ክፍሌም በዘርፉ ተጠቃሽ ሰው ነው። ይህ ሰው የፍጹም የቅርብ ኃላፊ ሲሆን፣ የኤርትራ የድንበር አካባቢና የምዕራብ ወታደራዊ ቀጣና አዛዥ ነው፡፡

አድሚራል ሁመድ ካርካሬም ይህን ስራ በማከናወን ይታወቃል። አድሚራሉ የኤርትራ የባህር ሃይል አዛዥ ነው፡፡ ለጅቡቲው ተቃዋሚ "ውህደት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባር" (ፍሩድ) ቀጥተኛ ድጋፍም ያደርጋል። ከስልጠና ጋር በተያያዘም ኤርትራ የውጭ ዘመቻዎቹን ለማከናወን ትችል ዘንድ ሰፊና ውስብስብ የስልጠና ማዕከሎችን ካምፖችንና ግብዓቶችን አሟልታለች፡፡ ብሔራዊ የደህንነት ኤጀንሲው ለውጭ ተቃዋሚ ሃይሎች ስልጠና በሚያዘጋጅበት ወቅት፣ የሥልጠና ግብዓቶችን፣ ሎጀስቲክስንና ቁሳቁሶችን የሚያቀርበው ደግሞ ወታደራዊ ማዕከሉ ነው፡፡

አጣሪ ቡድኑ የሥልጠና ግብዓቶችን በተመለከተ መረጃ ማሰባሰብ በማቀድ ከ6 ተቃዋሚ ታጣቂ ቡድኖች የቀድሞ አባላት ጋር ቃለ- መጠይቅ አድርጓል፡፡ እነርሱም አል- ሸባብ ፣ሂዝቡላ ኢስላም/የሶማሊያ እስላማዊ ግንባር፣ ሂዝቡላ ኢስላም/ኤአርኤስ አስመራ፣ ኦብነግ፣ ኦነግ እና ውህደት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባር(ውአዴግ) (FRUD) ናቸው፡፡

ከእነዚህ አባላት የተሰበሰቡ መረጃዎች ወጥነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስልጠናው የተሰጠባቸው ስፍራዎች የዋና ዋና አሰልጣኝ መኮንን ስሞች በተለይም በመሃል እና ምስራቅ ኤርትራ የተሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ በቃለ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎች ይመሳሰላሉ፡፡ ይሁንና በተወሰኑ ስልጠናዎችና የግብዓች አቅርቦት ዙሪያ የኋላ ኋላ ልዩነት ይታይባቸው ነበር፡፡ አጣሪ ቡድኑ በሥራ ዘመኑ ኤርትራ በቀጣናው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖችን በመርዳት ላይ መሰማራቷን ተገንዝቧል፡፡ ኤርትራ ለእነዚህ ኃይሎች የሚታደርገው ድጋፍ በግርድፉ በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

አንደኛው ውሣኔ 1844 (2008) እና 1907 (2009) በመጣስ ለሶማሊያ ታጣቂ ተቃዋሚዎች የሚደረግ ድጋፍ፣ ሁለተኛው ውሣኔ 1844 (2009) እና 1907 (2009) በመተላለፍ በሶማሊያ አማካኝነት የኢትዮጵያ ታጣቂ ተቃዋሚ ቡድኖችን ለመርዳት የሚደረግ ዕርዳታ፣ ሶስተኛው ውሣኔ 1907 (2009) በመተላለፍ ሶማሊያዊ ባልሆኑ ሰዎች

የተቋቋሙ ተቃዋሚ ታጣቂ ቡድኖችን በመርዳት የሚደረጉ ጥሰቶች ሲሆኑ፣ አራተኛው ደግሞ በኤርትራ አገዛዝና ቁጥጥር ስር የዋሉ ሃይሎችን እንደ የውስጥ ተቃዋሚ ቡድኖች አድርጎ በሃሰት በማደራጀትና ውሳኔ 1907 (2009) መጣስ ናቸው።

ይህን ተከትሎም የጂብቲና የኤርትራ የጋራ የባህር ዳርቻ አዋሳኝ በሆነችው ራስ ዱመይራ አቅራቢያ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ሰኔ 2008 ጦርነት ፈነዳ። በዘመቻው ጂቡቲ 30 ወታደሮች ሲገደሉባት፣ 19 እንደቆሰሉና ሌሎች በርካቶች እንደጠፉባት ገልጻለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጂቡቲ ሁለት ኤይርክራፍቶችን ጨምሮ በርካታ ተሽከርካሪዎችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ጥይቶች፣ የጦር መሣሪያዎችና ወታደራዊ ቁሳቁሶች እንደወደሙባት አስታውቃለች፡፡ የኤርትራ መንግስት ግን ስለግጭቱ ያለው ነገር የለም፡፡

ምንም እንኳን ሁለቱ ሀገሮች በኳታር አደራዳሪነት ሰኔ 9 ቀን 2010 በይፋ የተኩስ አቁም ስምምነት ቢፈራረሙም፣ ኤርትራ ከ “ውህደት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባር” (ፍሩድ) ተገንጥሎ የተመሰረተውን ተቃዋሚ ድርጅት መርዳቷን ቀጥላበታለች፡፡ ውህደት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባር-ሐ (FRUD -C) ነዋሪነቱ ፈረንሳይ ሀገር በሆነው ሞሃመድ ኪድአሚ በሚባል የአፋር ፖለቲከኛ ግለሰብ የሚመራ ተቃዋሚ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ ጅቡቲ ውስጥ በአቦክ እና በታጁራ መሃል በሚገኘው በማብላ ተራራ መሽጎ ወታደራዊ ዘመቻዎችን በማድረግ በጅቡቲ ጦር ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡ እንደ ጅቡቲ ባለስልጣናት ገለፃ ከሆነ፣ ድርጅቱ ራሱን የሚያስተዳድረው በዘረፋ ነው፡፡

አማፂው የአፋር ጎሣ ንቅናቄ (ውአዴግ-ሐ) ከህዳር 1991 እስከ ታህሳስ 1994 ድረስ በጅቡቲ መንግስት ላይ ሰርጎ ለመግባት ጦርነት አውጆ ነበር፡፡ ወቅቱ የድርጅቱ አንጃዎች ከመንግስት ጋር የሠላም ስምምነት ያደረጉበትና ሁለት አባላቱን በካቢኔነት እንዲቀላቀሉ የፈቀደበትም ነበር፡፡ በአህመድ ዲኒ አህመድ መሪነት አንጃዎቹ የትጥቅ ትግሉን ለመቀጠል ሞክረው ነበር– ሁለተኛው የሠላም ስምምነት ፓሪስ ውስጥ እስከ ተፈረመበት የካቲት 7 ቀን 2000 ድረስ፡፡

ከ2000 እስከ 2008 ድረስ ባለው ጊዜ የውህደት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባር-ሐ (ውአዴግ-ሐ) ፀረ-መንግሥት ዘመቻዎች የድርጅቱ ቃል አቀባይ ሞሃመድ ሃሰን ሙቅቢል ከሚያስተላልፈው መልዕክት ባለፈ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። በ2009 ግን ኤርትራ

የድርጅቱን ማዛዥ ጣቢያ፣ ስልጠና የጦር መሣሪያና ትጥቅ ልታሟላለት ፕሮግራም ነደፈች፡፡

ከ2008 ጀምሮ ኤርትራ ለ"ውአዴግ-ሐ" የምታደርገው እርዳታና ድጋፍ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበረነና በአብዛኛውም ውጤታማ ያልነበረ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን፤ኤርትራ ለቡድኑ ስታደርግ የነበረው ድጋፍ የፀጥታውን ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1907(2009) የሚጥስ እንዲሁም የውሳኔ ቁጥር 1862 (2009) ተፈፃሚ እንዳይሆን እንቅፋት የፈጠረ ነው። በጅብቲ እስር ቤት የሚገኘው የቀድሞ ውአዴግ-ሐ አዛዥ መሃመድ ጃብሃ ከአጣሪ ቡድኑ ጋር ቃለ መጠይቅ ባደረገበት ወቅት እንደተናገረው፤ ሚሊሻዎቹ ከ2008 ጀምሮ ከኤርትራ ድጋፍ ያገኙ ነበር፡፡ የጅበሳ ታጣቂዎች በአሳይባና ቡሬ መሃል የሚገኘውን የኤርትራ ወታደራዊ ማዕከል እንዲገለገሉበት ተፈቅዶላቸው ነበር፡፡

በኤርትራ ጅቡቲ አዋሳኝ ድንበር ጦርነት በተቀሰቀሰ ጊዜ ደግሞ የውአዴግ-ሐ ጦር ማዘዣውን ወደ ዴባሲም አዛውሯል፡፡ በ2009 ደግሞ ወደ እንዳ አሊ ወስዶታል፡፡ የጅቡቲ መንግስት የሰበሰባቸው መረጃዎች እንደሚያስረዱት፤ መሐመድ ጃብሃ ለታጣቂዎቹ የጦር መሣሪያ፣ ጥይትና የትጥቅ አቅርቦት የሚያገኘው ከኤርትራ መንግስት መሆኑን ተናግሯል፡፡

ይሁንና መሐመድ ከአጣሪ ቡድኑ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ፤ የኤርትራ መንግስት "ምግብ፣ መድኃኒትና የቆሰሉ ወታደሮችን በማከም ረድቶናል" በማለት የጦር መሣሪያና የትጥቅ ትግል ዕርዳታ እንዳልተደረገላቸው አስተባብሏል፡፡ ቡድኑ ወታደራዊ ልብሶችን ፣ የጦር መሣሪያዎችንና ጥይቶችን ከየመን ለመግዛት እንደተገደደም ጠቁሟል፡፡ ማዕከሉን አሰብ ካደረገው የኤርትራ ወታደራዊ የደህንነት መኮንን ከሆነው ኮሎኔል ሃፃይነት ጋር ብዙ ጊዜ እንደተገናኘም መስክሯል፡፡

የኤርትራን ቀጣናዊ አዋኪነት ከኢትዮጵያ አኳያ ስንመለከተው ደግሞ፤ ኤርትራ የኦጋዴን ነጻነት ግንባር መርዳት የጀመረችው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ መሆኑን አጣሪ ቡድኑ ቀደም ባሉት ዘገባዎቹ ማመልከቱ እናስታውሳለን፡፡ ከአስመራ ጋር በተደረገ የመጀሪያዎቹ ግንኙነት የተሳተፈ አንድ የኦብነግ ባለስልጣን ለአጣሪ ቡድኑ እንደገለጸው፤ የመጀመሪያው የኦብነግ መልዕክተኛ ከፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ባለሥልጣናት ጋር የፊት ለፊት ውይይት በማድረግ ወደ አስመራ የመጣው

በ2011 ነበር፡፡ በአጣሪ ቡድኑ የደረሱ አዳዲስ መረጃዎች እንደሚገልጹት ወሳኔ ቁጥር 1907 (2009) ከተላለፈ ወዲህም ቢሆን ይህ የኤርትራ ድጋፍ አልተቋረጠም፡፡

ከቀደምትና ከአሁኖቹ የኦብነግ ከፍተኛ አመራሮች የተገኙ መረጃዎች ደግሞ ከ2006 ቀደም ባሉት ዓመታት፤ ኦብነግ ከኤርትራ ጋር የሚገናኘው በዋነኛነት በቦሳሶና የመሃል ሶማሊያው አብዱቅ ከዚያም የኢትዮጵያን ድንበር በማቋረጥ ነበር፡፡ ለዚህ ስምሪት ሎጀስቲክስ እንዲያቀርቡ ከተመደቡት መካከል በኤርትራ መንግስት በኩል ኮሎኔል ጠዓመ (ወዲ መቀሌ) /የጄኔራል ማዕረግ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ/ እና ኮሎኔል ተወልደ ሃብቴ ነጋሽ ሲሆኑ፤ ከኦብነግና በኩል ደግሞ አብዲኑር ሶያን እና በሽር ማክታል ይጠቀሳሉ። የጦር መሣሪያዎችና ተተኳሾች የሚመጡትም በቀጥታ ከኤርትራ ነበር፡፡

ከ2007 እስከ 2008 ድረስ ግን ኤርትራ ለየመን ክፍያ እየፈጸመች መሣሪያ ለኦብነግ የምታስገባበት ሥርዓት ተዘርግቷል። ይሁን እንጂ ከየመን የሚገባው ቁሳቁስ ደረጃውን የጠበቀ እንዳልነበረ ተገልጿል፡፡ የእስላማዊ ህብረት ፍርድ ቤቶች ሞቃዲሾን ከተቆጣጠረበት ከ2006 ጀምሮ ኦብነግና እስላማዊ ህብረት ፍርድ ቤቱ ቀጥተኛ ወታደራዊ ትብብር እስከተፈራረመበት ጊዜ ድረስ ኤርትራ በእስላማዊ ህብረት ፍርድ ቤቱ ርዳታ የምትሰጠው ከኦብነግ ጋር በተገናኘበት ስልት ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም የኦብነግ ባለስልጣን በሽር ማክታልና የኤርትራ ስላላ መኮንን ተወልደ ሃብቴ ወደ ሞቃዲሾ አቅንተዋል፡፡

በ2006 ኢትዮጵያ ለደህንነቷ ስትል ሶማሊያ በመግባት የእስላማዊ ህብረት ፍርድ ቤት ህብረትን ያስወገደች ሲሆን፤ ኤርትራ ለኦብነግ የምትሰጠውን ድጋፍ በፑንትላንድ በኩል እንድታደርግ አስገድዶታል፡፡ ይሁንና የኢትዮጵያ የስለላ አገልግሎት ከፑንትላንድ ባለስልጣናት ጋር በመሆን በ2008 አብዲ ኑር ያሲንን ጨምሮ በርካታ የኦብነግ ባለሥልጣናት በኢትዮጵያ እጅ እንዲወድቁ አድርጓል፡፡ ዘመቻው ኤርትራና ኦብነግ ሌላ የግንኙነት አማራጭ እንዲጠቀሙ አስገድዷቸዋል፡፡ እናም ኦብነግ ዋነኛ የአቅርቦት መስመሩን ወደ ምዕራብ ሶማሌላንድ አውዳል ክልል ማዛወር ግድ ብሎታል፡፡

እናም በመስከረም 2010 መግቢያ ላይ ከ200 ባላይ የኦብነግ ታጣቂዎች በባህር ተጉዘው በሶማሌላንድ ደቡብ ምዕራብ አቅራቢያ የምትገኘው የወደብ መንደር (ሉግሃያ) ደረሱ፡፡ ይህ የኦብነግ ቡድን ዓላማው በሶማሊያ ተሽሎክሉከው በማለፍ ወደ ኢትዮጵያ

የድንበር ከተማ ቦራሜ መግባት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የሶማሌላንድ የደህንነት ሃይል ስላገኛቸው ወደ ኢትዮጵያ በኩል እንዲሸሹ አስገደዳቸው፡፡ ከዚያም የኢትዮጵያ ሰራዊት ጥቃት ስለከፈተባቸው ተበታተኑ፡፡

ታዲያ ከዚህ ጥቃት ተርፈው ጅግጅጋ በእስር ላይ ከሚገኙ የኦብነግ አባላት ጋር አጣሪ ቡድኑ ቃለ መጠይቅ አድርጎ ነበር፡፡ ቡድኑ ከሁለቱም ግንባሮች የተሰበሰቡ የጦር መሣሪያና ትጥቆችንም አግኝቷል፡፡ ከዚህ ጥናት መረዳት እንደሚቻለው፤ የኦብነግ ታጣቂ በኤርትራ ለመሰልጠኑና ለመታጠቁ እንዲሁም መነሻውና ማዘዣ ጣቢያው ይህችው ሀገር መሆኗ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ እናም ኤርትራ ይህን ታጣቂ ቡድን መርዳቷና የሶማሊያን ድንበር አቋርጦ እንዲጓዝ መፍቀዷ ሁለቱንም የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎች 1844 (2008) እና 1907 (2009) ተላልፋለች፡፡…

…ውድ አንባቢዎቼ የፀጥታው ምክር ቤት የኤርትራንና የሶማሊያን ጉዳይ እንዲያጠና የመደበው አጣሪ ቡድን ከቀጣናው አንፃር ያጠናቀረው ዘገባ እጅግ ብዙ ቢሆንም፤ እኔ ለግንዛቤ ያህል ያቀረብኩላችሁን የክፍል አንድ ትርክቴን በዚህ እቋጫለሁ— በቀጣዩ ክፍል ምልከታዬ በሌሎች ጉዳዮች እስክመለስ ድረስ።…